በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሐምሌ 6 ቀን 2011 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የምረቃ በዓል ላይ ያደረጉት ንግግር

ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጐች እንደእናንተ ፈንድቀው ተደስተው የምናይብት ዘመን ይመጣል።

ክብር ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ የከፍተኛ ፕሬዘዳንት

ክቡር ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና የአዲስ አበባ ዩኒቪርሲቲ ፕሬዘዳንት

እጅግ የተወደዱ የተከበሩ የዘመናችን ድንቅ አባት ሙፍቲ ሀጂ ዑመር

የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ዩኒቪርሲቲ የቦርድ አባላት፣ የሴኔት አባላት፣ መምህራን እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች

ከሁሉ በላይ ለዚህ ድንቅ ቀን ዋነኛ ባለቤት የሆናችሁ ወላጆች እንዲሁም ጣፋጭ ህልምና ታላቅ ግብ በጥረታችሁ ዛሬ እውን ያደረጋችሁ ውድ ተመራቂዎች እንኳን ደስ ያላችሁ።

በኑሮ ቀንበር ሳትጐብጡ፣ በውጣ ውረድ ሳትደናቀፉ፣ የመጨረስን ጣፋጭ ጣዕም ቀምሳችሁና አጣጥማችሁ ለትውልድ መጨረስ እንደሚቻል በተግባር ያስተማራችሁ የእለቱ ሙሽሮች በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ።

ደስታችሁ እንዲውል፣ ደስታችሁ እንዲያድር፣ ደስታችሁ እንዲከርም፣ ደስታችሁ ለዜጐቻችን ሁሉ እንዲጋባ ያለኝን ታላቅ ምኞት ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ። ትልቁ የዕውቀት መሸመቻ ምክራብ ዩኒቨርሲቲ ቢሆንም የሰው ልጅ ሁሌም እንደ አዲስ በየዕለቱ ከበላይና ከበታቹ ከተፈጥሮ እንደ ተማረ የትምህርትን መጨረሻ ሳያይ ይዘልቃል። ነገር ግን በዩኒቨርሲቲ ያውም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መመረቅ ያለውን ክብር ከጥቂት አመታት በፊት ቀምሼ ስለማውቀው ከእናንተ ፊት ሆኜ በዚህ የምርቃት ስነስርዓት ንግግር ላደርግ በመቻሌ እና የደስታችሁ ተጋሪ በመሆኔ የተሰማኝን ልዩ ክብር ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ።

እጩ ተመራቂዎች በተለይም ወጣቶች ከፊታችሁ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ይጠብቃችኋል። የትዳር ዩኒቨርሲቲ ይጠብቃችኋል። ይህ የትዳር ዩኒቨርሲቲ ከዋን ኦዋን የሚጀምር አይደለም። የፈተና ስርአቱም እዚህ እንደለመዳችሁት አይደለም ነገር ግን እሱም መውደቅም መመረቅም አለው ከትዳር ዩኒቨርሲቲ። በተጨማሪ የስራ ዩኒቨርሲቲ በስራ አለም ውስጥ ከታላላቅዎች ከሴቶች ከወንዶች ልምድ ካላቸውና ከሌላቸው ሰዎች ጋር ሰርቶ ውሎ ለመግባት አዲስ ልምምድ የሚጠይቅ እሱም እንዲሁ መመረቅና መውደቅ በውስጡ ያለ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ።

እንዲሁም የህይወት ፈተናን ተጋፍጣችሁ በጥሞና በማስተዋል ከአካባቢያችሁ የምትማሩበት የፈተና ሂደቱ በውጤት የሚለካበት ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ። እስከ ዛሬ የሚሰጣችሁን ኮርስ በላቀ ውጤት ለማምጣት የማንበብ ልማዳችሁ ተቀይሮ ከምትማሩት ሳብጀክት ውጪ አዳዲስ ፅሁፎች፣ አዳዲስ ሀሳቦች ለማንበብ ለማወቅ የምትለማመዱበት ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ። ሌሎች ያልጠቀስኳቸው በርካታ የህይወት ልምድና ትምህርት የሚወሰዱባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ከፊታችን ያሉ ቢሆንም የመመረቂያ ስነ ሥርዓቱ ግን ዛሬ ከምናየው የተለየ ነው። የምትለብሱት ጋዎን፣ አቀማመጣችሁ፣ የዲፓርትመንቶች ፉክክር እንዲሁም የላቀ ጥረትና ውጤት ያመጡ ሰዎች የመጨረሻውን የደስታ ፅዋን የሚቀምሱበት ይህ የምርቃት ስነስርዓት ከሁሉም የተለየ የሚያደርገው በዩኒቨርሲቲ በመሆኑና በአንድ ጊዜ ዘጠኝ ሺ ሰዎች የሚመረቁበት መሆኑም ጭምር ነው።

ይህ ምርቃት የተለየ የሚያደርገው በዩኒቨርሲቲ መማራችሁ ሲሆን ዩኒቨርሲቲ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ማንሳት ጠቃሚ ይሆናል። ዩኒቨርሲቲ ማለት በላቲን ቋንቋ የተሟላ ማለት ነው። አንድ ሰው ወደ ሙላት የሚያድግበት ተቋም ማለት ነው። ወደ ሙላት ለማደግ ማወዳደር የግድ ነው። ወደሙላት ለማደግ ማነፃፀር ይጠይቃል። ወደሙላት ለማደግ ማስተያየት፣ ማገናዘብ አመዛዝኖም የጐደለ ለይቶ አክሎ መሙላት ይጠይቃል። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ አንድ የምትወዱትን ሰው ትምህርት ተምሮ መመረቅ አይቻልም። የአንድ ሰው መፅሐፍ አንብቦ ፕሮጀክት መፃፍ አይቻልም። ከተለያየ ፐርስፔክቲቭ የተለያየ እይታን ማየትና ማገላበጥ መሞገት ማመዛዘንና የላቀውንና የተሻለውን አስበልጦ መውሰድ ይጠይቃል። ለዚህ ነው ወደሙላት የሚታደግበት የተሟላ ተቋም ያሉት የያኔው ዋይዝ የላቲን ምሁራን።

እንዲሁም ግራጁዌሽን ማለት በመካከለኛው የአውሮፓ ዘመን ቋንቋ የተለመደ መሆኑና ስርወ ቃሉ ከላቲን እንደመጣ እየተዘነጋ ያለ ቢሆንም ግራጅዌት ማድረግ ወይም ግራጅዌሽን ማለት እላይ መውጣት ማለት ነው። መላቅ ማለት ነው። መሻል ማለሻል ማለት ነው። ከነበረው ዩኒቨርስቲ ከእናንተ ጋር ከገባው ሰው ሁሉ ልቃችሁ ተሽላችሁ መመረቃችሁን በኩራት ልመሰክርላችሁ እፈልጋለሁ። ነገር ግን የአማርኛው ግራጅዌሽን ከላቲኑ ወይም በመካከለኛው ዘመን አውሮፓውያን ከሚተቀሙበት ግራጅዌሽን በእጅጉ የላቀ ነው። ለጭንቅላት ብቻ ሳይሆን ለመንፈስም፣ ለውስጥ ማንነትም ትምህርት አለው። መመረቅ ማለት መባረክ ማለት ነው። መመረቅ ማለት ባዩህ ባዩሽ፤ በቀመሱህ፤ በለኩህ ሰዎች ታምኖብህ ይበል ይሁን ተሽለሃልና ይፅደቅልህ ማለት ነው። ይህንን ምርቃት ለማዝለቅ ገፌ ሃይል ሆኖ እንድንማር ያደረገንን ነገር በተወሰነ ደረጃ ማንሳት

እፈልጋለሁ። አንድ ሰው ለማወቅ፣ ለመላቅ ወደሙላት ተቋም ገብቶ አዳዲስ ዕውቀት ሲገበይ፤ ፕራይመርሊ ደራይቪንግ ሞቲቬሽኑ ምንድን ነው? ዋናው ለመማር ገፊ የሆነው ሀይል ምንድን ነው? የሚለውን ማወቅ በእጅጉ ያስፈልጋል። ሰዎች ለመማር ለማወቅ ለመላቅ የሚያደርጉትን ጥረት የተለያየ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጠውታል። ሁሉም ምሁራን ለመማር የሚደረገውን ገፊ ሃይል ተመሰሳይ የሆነ ትርጓሜና ብያኔ አልሰጡትም። ለምሳሌ ፍሬድሪክ ኒቼን ብንወስድ ሰው ለመማር ለመጣር ለመላቅ የሚያደርገው ገፊ ሃይል ዊልቱ ፓወር (will to power) ነው ይለዋል። የመግዛት መሻት ነው ይለዋል። ሌላውን ለመግዛት ሌላውን ለማሸነፍ ከሌላው ለመላቅ ነው ሰው አልትሜትሊ መማር የሚፈልገው ብሎ ያስባል። ፍራንሲስ ፉክያማ ይህንን ከግለሠብ ወደ ግሩፕ ሲወስደው ሜጋ ኦቶሚያ ይለዋል። ሜጋ ኦቶሚያ ዲፋይን ያደረገው በበላይነት በገዢነት የመኖር መሻት ነው ለመማር ገፊ ኃይል የሆነው ይላል። ነገር ግን የሰው ልጅ ዘላለማዊ አይደለም። ለዘላለም አይኖርም። ለዘላለም መግዛትም አይችልም። በመሆኑም የሁሉም ሰው ፍላጐት መግዛት ነው የሚል ትርጓሜ ትክክል አይደለም ብለው የሚሞግቱ ሌሎች ምሁራን አሉ። ከነዚህ መካከል ጀርሚ ቤንተሃም ሚጠቀስ ምሁር ነው።

ጀርሚ ሰው ለመማር ገፊ ሃይል (push factor) የሃሴት ጥማት ነው ይለዋል። የመግዛት ፍላጐት ሳይሆን ዊል ቱ ፕሌዠር ነው ይለዋል (will to pleasure) ነው ይለዋል። ለደስታ የራስን ደስታ ለመሸመት ሰው መማር እንደሚፈልግ የሚገልፀው ጀርሚ የሰው ልጅ ደስታውን ለማግኘት የማይከፍለው ዋጋ የለም ይለዋል። ለመደሰት ይሰርቃል፣ ለመደሰት ይገድላል፣ ለመደሰት ይቀማል፣ ደስታውን ለማግኘት ማንኛውንም ዋጋ ይከፍላል። ይህንንም የወንጀል ህግ መሠረቱ ምን እንደሆነ ጉን ለጉን ለማሣየት ምሁራን ሲሞክሩ ወንጀለኛው ወንጀል በመሥራት ከሚያገኘው ደስታ ይልቅ ቅጣቱን በማክበድ፣ የቅጣቱን ህመም፣ የቅጣቱን ስቃይ ማግዘፍ ወንጀሉን ለመቀነስ ፋይዳ እንዳለው ይገልፃሉ። ወንጀልን የምንቀንስበት የቅጣት ህመሙ ጠንከር ያለ ካልሆነ ሰው ደስታውን ለመሸመት ሲል የማያደርገው ነገር እንደሌለ የጀርሚ ቤንታሚን ህሳቤ በመደገፍ ሃሳብ ይሰነዝራሉ። ሌሎች ምሁራን ደግሞ የሚቃወሙ አሉ ወይም የተለየ ሃሳብ ያራምዳሉ ከነዚህ መካከል አንዱ ቻርለስ ዳርዊን ነው።

ዳርዊን ዊል ቱ ሰርቫይቭ (will to survive) ነው ይለዋል። ሰው ስርቫይቭ ለማድረግ ሲሻው እያባላ አልያም እየበላ የራሱን ሰርቫይቫል ብቻ ለማረጋገጥ የሚጥር ነው ይለዋል። ለሰርቫይቫል ሲባል መብላት ለሰርቫይቫል ሲባል ማባላት ግን እስከመቼ? ሰው ኢተርናል ላፍ እንደሌለው እያወቀ ለመብላት የሚያባላ ለመብላት የሚበላ ከሆነ በዘላቂነት ሰርቫይቫልን እውን ማድረግ ስለማይቻል ይህም ትክክል አይደለም ብሎ ቢሞግተው ቪክቶር የሚለው ምሁር ሰው ለመማር የሚገፋው ዋናው ሃይል ዘዊል ቱ ሚኒግ ነው ይለዋል። ትርጉም ላለው ነገር ነው ለመኖር ነው ሰው የሚማረው ብሎ ይተረጉመዋል። ይህ ትርጉም ያለው የመኖር ዘዬ ማለት መስጠት ነው። ማፍቀር ነው። መውደድ ነው። ማገልገል ነው። ሰዎች በመስጠት የሚያገኙትን ደስታ በመግዛት ሊያገኙት አይችሉም። አልትሜት የደስታ ምንጭ ከራስ አልፎ ለወገን ማድረግ መቻል በመሆኑ የቪክቶር እሳቤ ለእኛ ጠቃሚ ቢሆንም መልካምነትን፣ ደግነትን፣ ፍቅርን በምን መለካት ይቻላል? አንድ ሰው አንዲ

ኪሎ ስኳር መግዛት ቢፈልግ ሌላ አንድ ኪሎ ክብደት ያለው መዳብ፣ ብረት፣ ነሐስ ወይም ድንጋይ በአንድ ጐን አስቀምጦ በሌላ ወገን ስኳሩን እያስቀመጠ አንዲ ኪሎ መሆኑን መለካት ይችላል። አንድ ኪሎ ስኳር ለመለካት አንድ ኪሎ ሚመዝን ክብደት ያለው ሌላ ነገር ከሌላው አቅጣጫ ያስፈልጋል። ወይም አንድ ሌትር ውሃ ዘይት ለመለካት የፈለገ ሰው ያን መለካት የሚያስችል እቃ መያዝ ይኖርበታል። መልካምነትን፣ ፍቅርን፣ ደግነትን፣ መስጠትን በምን መለኪያ ልንለካው እንችላለን? መልካምነትንና ደግነትን የምትሰጡ ሰዎች በዛኛው ወገን የሰጣችሁት ካልተለካ ችግሩ እናንተ ጋ አይደለም። ሰውዬው ጋ መለኪያው የለም ማለት ነው። መሰላቸት ተስፋ መቁረጥ ማኩረፍ ሳይሆን የመልካምነት ሚዛን የመልካምነት መመዘኛን መጐናፀፍ እንዲችል አበክራችሁ መስራት ይኖርባችኋል። መልካምነት ያላችሁ ሰዎች መልካምነት በሚዛን የማይለካ ስለሆነ ሁሌ በመስጠት ሁሌ፣ በማፍቀር ሁሌ በመተግበር ብቻ እውን እንዲሆን ብዙ ጊዜ ካለፋችሁ በኃላ የሚነገር መሆኑን አውቃችሁ ዛሬም ነገም መልካም መሆንን በተለይ ለዚህች ድንቅ አገር መልካም መሆንን እንደክብር መውሰድ ይኖርባችኋል።

ውድ ተመራቂዎች ትላልቅ ዛፍ መቁረጥ የሚችል መጥረቢያ ምንም ያህል የተሞረደ የተሳለ ቢሆን፣ ምንም ያህል ባማረ መንገድ የተሠራ ቢሆን ከተናቀ አንድ ዱላ ከመዛቢያው ጋር መዋደድ ካልቻለ መጥረቢያውን ብቻ ይዞ ግንድ መቁረጥ አይቻልም። መጥረቢያው ብቻውን ዛፍን ቢመታ የሚሰበር ቁመቱ አጭር ውፍረቱም መካከለኛ የሆነ ዛቢያ ያስፈልገዋል። ዛቢያን ሳይንቅ ከዛቢያ የተዋደደ መጥረቢያ ትላልቅ ዛፍ መቁረጥ ይችላል። እናንተ የተማራችሁ ያወቃችሁ እራሳችሁን አሸንፋችሁ የተሰጣችሁን ፈተና አልፋችሁ የተመረቃችሁ ድንቅ ምሩቃን፤ ካልተማረው ህዝብ ጋር ካልተዋደዳችሁ በስተቀር ፍላጐታችሁን ማሳካት አትችሉም። የእናንተ መጠረብ የእናንተ መዘጋጀት ብቻውን ምንም የሚመስለውን ዛቢያ መርጦ መዋደድ ይሻልና በየሄዳችሁበት ባይማርም ካስተማራችሁ ባይኖረውም ቁርሶ ከሰጣችሁ ማህበረሰብ ጋር ተዋዳችሁ ኢትዮጵያን ማላቅ፣ ማስቀጠል የሁላችሁ የነገ ተልዕኮ እንደሆነ በዚሁ አጋጣሚ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

በቅርቡ አራት ቢልየን ትሪ በኢትዮጵያ በዚህ ክረምት ለመትከል ስራ ጀምረን ነበር። አራት ሚሊየን ትሪ ለመትከል ስንወስን የተሳለው የተጠረበው መጥረቢያ ዛቢያው ከሌለ ብቻውን እንደማያሳካው ስለሚያውቅ ይህንን ቅዱስ ሀሳብ ለመላው ህዝብ በቀረበው ጥያቄ መሰረት እስከ ዛሬ ድረስ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊየን በላይ ዛፍ ተክለናል። አንድ የአውሮፓ ሀያል ከሚባሉ የአውሮፓ አገራት መካከል አንዱ የውጭ ጉዳይ ከትናንትና ወዲያ ደውሎልኝ በእኔ አገር በሙሉ አራት ቢሊየን ዛፍ የለም አንተ በአንድ ክረምት አራት ቢሊየን ዛፍ እተክላለሁ ብለህ ማሰብህ ትልቅ ነገር እንደምታስብ ያሳያልና ምን ላግዝህ ሲለኝ ፕሮግራሙን ለማስፈፀም አንዳንድ ነገር ያስፈልጋል ብዬው መቶ ሰላሣ ሚሊዮን ዩሮ እርዳታ ሰጠን። ትልቅ ሀሳብ ትልቅ ሆኖ ትልልቆቹን ኮንቬንስ የሚያደርገው ሲተገበር ነው። አራት ቢሊየን ብለናል አራት ቢሊየን የምናደርግ ህዝቦች መሆናችንን፣ ትላልቅ ማሰብ ትላልቅ መከወን የምንችል መሆናችንን ለአለም ስናሳይ ደህነትንም እንደዚሁ አሸንፈን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ መሆናችንን ዳግም እናረጋግጣለን።

ውድ ተመራቂዎች ስንኖር ኢትዮጵያዊ ከሆንን ኢትዮጵያችን ግሪን መሆን አለባት። ስንሞት ኢትዮጵያ ከሆን ቢያንስ መቃብራችን በጥላ ስር በዛፍ ስር መሆን አለበት። ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ከሆን ቢያነንስ ልጆቻችን ድህነትን ዳግም የማያስተናግዱ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ወቶ በጀት አንሶኛል የሚልበት ዘመን ማብቃት ይኖርበታል። ይህ እንዲሆን የተሳላችሁ የተጠረባችሁ የተዘጋጃችሁ ምሁራን ዛቢያውን ሳትዘነጉ ከዛቢያው ጋር ተዋዳችሁ ካልተማረው ካልተዘጋጀው ብዙዎች ከሚንቁት ግን ታሪክ ከሚሠራው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እጅና እጅ ሆነን ኢትዮጵያን ማስቀጠል ከማንም በላይ ከእናንተ የሚጠበቅ ይሆናል። አዲስ አበባ ላይ በዚህ ክረምት አራት መቶ አርባ ስምንት ትምህርት ቤቶች ለማደስ ስራ ተጀምሯል። ይህንን ስራ በመንግስት በጀት ቢሆን ኖሮ አምስት አመት አስር አመት ይፈጅብን ነበር። ምክንያቱም የጨረታ ህግ ስላለ ምክንያቱም የበጀት ስርዓቱ ውስንነት ስላለበት። ነገር ግን ብዙ ባለኃብቶች እና የበጐ ፍቃድ አገልጋዮች ወጣቶች ተባብረው አራት መቶ አርባ ስምንት ትምህርት ቤት ክረምቱን አድሰን፣ ብላክ ቦርድ ቀይረን፣ ወንበር ጠግነን አጥር ጠግነን ዛፍ ተክለን በንፅፅር ሻል ያለ ትምህርት ቤት ለልጆቻችን ለማዘጋጀት የምናደርገው ጥረት ሌሎች ትላልቅ ጉዳዮች ከተባበርን ማሰካት እንደምንችል ምስክር መሆን ይችላል። በዚህ ክረምት በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ስድስት መቶ ሺህ ታዳጊዎች ሰባት ነጥብ ሁለት ሚልየን ደብተር በዚሁ መንገድ እያዘጋጀንላቸው ሲሆን ተማሪዎች መስከረም ላይ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ለእያንዳንዳቸው ደብተር ሰጥተን፣ ለ ስድስት መቶ ሺ ተማሪ ዩኒፎርም አሰፍተን፣ ትምህርት ቤት አድሰን፣ አምና ጥለው የሄዱትን አስውበን ብናስገባቸው ከስድስት መቶ ሺው ስልሳ ሺው ቢሳካልን፣ ከስልሳው ሺ ስድስት ሺ ቢሳካልን፣ ከስድስት ሺው ስድስት መቶ ቢሳካልን፣ ከዚያም ስልሳ ቢሳካልን ቢያንስ ቢያን ስድስት ቢሳካልን፣ ስድስቱ ለኢትዮጵያ ብርሃን ሊሆኑ ይችላሉ። የዛሬው እያንዳንዱ ኢንቨስትመንት የጊዜ ጉዳይ እንጂ እራሱን አባዝቶ ሃብት ላፈሰሱ ጉልበት ላፈሰሱ ሰዎች መልስ መሆን ስለማይቀር የምንሰራው እያንዳንዱ ስራ ሲሰናሰል ሄዶሄዶ ኢትዮጵያን ውብ ኢትዮጵያን ከለማኝነት የሚያወጣ መሆኑን መገንዘብና መትጋት ከሁላችን ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪ በከተማ ውስጥ የሚገኙ ቅድም ፕሮፌሰር ጣሰው የገለፁትን ሆስፒታል ጨምሮ ከአስር በላይ የመንግስት ሆስፒታሎች በእድሳት ላይ ይገኛሉ። ብዙ ማህበረሰብ ለህክምና ሄዶ የሚቸገርባቸውን የህክምና ጣቢያዎች በማደስ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ በመንግስት ቢሆን አሁንም አድካሚና በአጭር ጊዜ የማይከወን ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከአንድ ሺ በላይ አቅመ ደካማ እናቶችና አባቶች የሚኖሩበትን ቤት አድሰን ክረምቱን ዝናብ ይዘንብብኛል ብለው ሳይሳቀቁ ዝናብ ሳይሆን የልጆቻቸውን ጉልበትና ሀብት ደስታ የሚሰጥ መሆኑን አምነው ለእናንተም ተጨማሪ ምርቃት የሚመርቁ እናቶች ለማስደሰት የተጀመረው ስራ ከአራት መቶ ሀምሳ ቤት በላይ እድሳት ተጀምሯል። አንድ ሺው በክረምት ይጠናቀቃል ።

ውድ ተመራዊዎች አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግር ይነገራል። ነጋጠባ መርዶ አለ። የሚያስፈራ ነገር አለ። ዛሬ ስትመረቁ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ሰባሰባት በማሪዎች ከኔጋር ከወሰናችሁ እና በልባችሁ አምናችሁ ካረጋገጣችሁ በእርግጠኝነት የምገልፅላችሁ ኢትዮጵያ አንድ ሆና ወደ ብርሃን የምትሻገርበት እንጂ ነገርዋ ወደ ኃላ የሚመለስበት ነገር አይኖርም። ይህ ውሳኔ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ይሆናል። ኢትዮጵያን ማፍረስ፣

ኢትዮጵያን ማሳዘን፣ ኢትዮጵያን መዝረፍ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም። ኢትዮጵያንም ቆፍራችሁ ብትጠይቋት ትነግራችኋለች። በዘመናት መካከል ብዙዎች ሞክረዋል። ሰዎች ገለዋል። ኢትዮጵያን ማፍረስ ግን አይቻልም።

ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያዊያን ውድና መከታ እንድንሆን ዛሬ በዚህ ታላቅ ዩኒቨርሲቲ የተመረቃችሁ ተማሪዎች ቀላሉን ሳይሆን ትክክለኛውን መንገድ መምረጥ ስትችሉ፤ ትርጉም ለሚሰጡ ነገሮች መኖር ስትችሉ፤ ስትመራመሩ፤ ስትጠይቁ፤ የመኖር ትርጉም ሲገባችሁ፤ የምላችሁ ኢትዮጵያ መፍጠር እንችላለን።

በዚህ አመት የኢትዮጵያ ጂዲፒ ከኬንያ ይበልጣል። በአስር ቢሊየን ገደማ ኢትዮጵያ ጂዲፒ ከኬንያ ጂዲፒ ይበልጣል። ነገር ግን የኬንያ የአመት በጀት ከኢትዮጵያ መንግስት በጀት በእጥፍ ይበልጣል። እኛ አስራ ሶስት ቢሊያን ዶላር ገደማ በጀት ብንይዝ ኬንያ ሃያ ሰባት ቢሊያን ገደማ በጀት ይዘዋል። ከጂዲፒያቸው አንድ ሦስተኛው ገደማውን ወይም የሚበልጠውን የመንግስት ወጪ አድርገው ይዘውታል። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ኢትዮጵያውያን በአለም ላይ በሚሊየን የሚቆጠር ዲያስፖራ ጉልበቱን፣ ጊዜውን፣ አልፎ አልፎ ምላሱን የሚጠቀም ዲያስፖራ በብዛት አላት። በተንደላቀቀ ሁኔታ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ብዙ ላይሆኑ ይችላሉ። ብዙዎቹ ለፍተው ጥረው ግረው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እሚያግዙ መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአመት እያንዳንዱ ዲያስፖራ አምስት ሺህ፣ በስድስት ወር ሁለት ሺ አምስት መቶ፣ በሦስት ወር ሰባት መቶ ብር ሂሳቡን ለእናንተ ትቼ ማዋጣትና የጋራ ኩባንያ መፍጠር ብችል አምስት ሺ ዶላር አንድ ሰው ካወጣ አንድ ሚሊየኑ አምስት ቢሊየን ሁለት ሚሊየኑ አስር ቢልየን ዶላር ማውጣት ይችላሉ በዓመት ማለት ነው። ስጦታ አይደለም ኢንቨስትመንት ነው። በየአመቱ አስር ቢልየን ዶላር ዲያስፖራ ወደኛ ጂዲፒ ኢንጀክት ካደረገ በየአመቱ ምን ያክል እድገት እንደምናመጣና ባጠረ ጊዜ ከአፍሪካ ትላልቅ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት ተርታ እንደምንመደብ ሂሳቡን ኢኮኖሚስቶች ከእኛ የተሻለ ማስላት ይችላሉ።

ለኢትዮጵያ ሳንሰጥ፣ ዕውቀታችንን ጉልበታችንን ጊዜአችንን ሳንሰጥ የምንመኛትን ኢትዮጵያ መፍጠር አንችልም። እምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የወሰነ በየትኛውም ሥፍራ ያለ ዜጋ ካለ ገንዘቡን ዱባይ ከሚያስቀምጥ፣ ገንዘቡን ለንድን ከሚያስቀምጥ፣ ገንዘቡን ቻይና ከሚያስቀምጥ፣ እነሱ የኛን ተቀማጭ ገንዘብ ኢንቨስት ከሚያደርጉ ኢትዮጵያዊያን በተባበረ መንገድ በህጋዊና ስርአት ባለው መንገድ ኢንቨስት ብናደርግ ባጠረ ጊዜ ኢኮኖሚያችንን ማሻሻልና ተመርቀው ስራ የሚያጡ ልጆቻችንን ስራ ለማስያዝ ሰፊ እድል ይሰጠናል። ነገር ግን የዛሬ ሰባ አምስት አመት ገደማ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንጉሡ ነገስቱ ቤት ስራ ሲጀምር የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በሁለት በሬና በሞፈር ያርሱ ነበር። ዛሬ ከሰባ አምስት አመት በኋላ አባትና እናቱን ከሞፈርና ቀንበር መገላገል ያልቻለ ትውልድ ቢማር ባይማር ምን ትርጉም አለው? ሌላ ሰባ አምስት አመት አንዳንቆይ ንስር ሆኖ የተፈጠረ አሞራ ጅግራ ሆኑ መሞት ስለሌለበት፤ የተማረ ኢትዮጵያዊ እንዲሁ በከንቱ መቶ በከንቱ ዲግሪ ቆጥሮ መመለስ ስሌለበት፤ በተባበረ ክንድ አርሶ አደሩ ከመድከም ከቀምበር ከበሬ ተላቆ በዘመነ መንገድ አርሶ በልቶ የሚያበላን እንዲሆንና ለማኘነት ከኢትዮጵያ እንዲወገድ በተባበረ ክንድና በዩኒቨርሳል ቫልዩ በጋራ እንድንሰራ በታላቅ ትህትና ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

ከእናንተ የሚፈለገው ነገር ወቶ ሰርቶ ገቢ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ የተማራችሁትን ዩኒቨርሳል ቫልዩስ የማህበረሰቡ ቫልዩ ማድረግ ነው፡፡ ዩኒቨርሳል እሴት በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በስፋት መኖር ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ስምንት ሜን ዩኒቨርሳላ ቫልዩ እሴቶች አሉ አንደኛው ክብር ነው፡፡ የሁሉንም አበርክቶ የሁሉንም እውቀት የሁሉንም ችሎታ ማክበርና በፀጋ መቀበል አንድ ዩኒቨርሳል ቫልዩ ተብሎ በዩኒቨርሲቲ ከሚታወቅ ነገር ነው፡፡ ሁሉንም ማክበር ማለት ከመሳደብ መቆጠብ ማለት ነው፡፡ ሁሉንም ማክበር ማለት ሌላው ወገን ጋር ቫሊዩ እንዳለ ማመን ማለት ነው፡፡ ይሄን ማስተማር ከእናንተ ይጠበቃል፡፡ ሁለተኛው ልህቀት ነው በምንሰራው ሥራ በጥናት በምርምር በመድከም የተሻለ ነገር ማምጣት መቻል ነው፡፡ ይህንን ከእናንተ አሳልፋችሁ ማህበረሰቡን ማስተማር ይጠበቅባችኋል፡፡ ሶስተኛው እሴት ትህትና ነው፡፡ ትሁት ስብዕናን መላበስ ነው፡፡ ሰው ትሁት ሆኖ ደካሞችን ማክበርና ማገልገል ሲችል ማዘንና፣ ማፍቀር ቢችል ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውም፡፡ ሚዛኑ ተመልሶ እራሱ በጉነት ስለሆነ በጉነት በኪሎ በጉነትን በሜትር በጎነትን በሊትር ሳንለካ ሁሌም በመስጠትና ትሁት በመሆን ማህበረሰባችንን መቅረፅና ማስተማር ከእናንተ ይጠበቃል፡ ፡ አራተኛው ዩኒቨርሳል ቫልዩ ሰርቪስ ነው አገልግሎት፡፡ ዛሬ ከዘጠኝ ሺ ምሩቃንተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ቢያንስ መቶሺ ችግኝ እንጠብቃለን ቤት ስትገቡ በእናንተ ግቢ ውስጥ በእናንተ ሰፈር ወይም በእናንተ ትምህርት ቤት ውስጥ አምስት አምስት አስር አስር ችግኝ ብትተክሉ ትልቅ የማገልገል ልምምድ ስለሆነ ዛሬ መጀመራችሁ ለነገ ፈር ቀዳጅ ስለሚሆን እንደ አንድ ማስተማሪያ መንገድ አገርና ህዝብ ለማገልገል ለትውልድ ራሳችሁን ለመስጠት እንደማሳያ ተጠቀሙበት፡፡ አምስተኛው እንግዳ መቀበል ነው በርካታ ቱሪስቶች ኢንቨስተሮች እየጋበዝን ነው፡፡ ኢንቨስተርና ቱሪስት መቀበሉ ቆይቶ ኦሮሞዎች ሳይቸገሩ በባህር ዳር፣ አማራዎች ሳይቸገሩ በመቀሌ፣ ትግራዮች ሳይቸገሩ በቦረና፣ በጉጂ ሲዳማዎች ሳይቸገሩ በሶዶ ጉራጌዎች ሳይቸገሩ፤ በወራቤ የሚንቀሳቀሱባትን ኢትዮጵያ እንፍጠር፡፡ ኢትዮጵያ ለመቶ ሚሊየን ኢትዮጵያ በቂ ናት ኢትዮጵያ መቶ ሚሊየን ኢትዮጵያዊ ከተባበረና ከተደመረ አንቀባራ መኖር ትችላለች፡፡ ግሪድ ንፉግነት ኖሮ አንተ የኔ አይደለህም የሚልን ሀሳብ ግን ኢትዮጵያን ትንሽ ስለሚያደርግና ኢትዮጵያ ካነሰች የዛሬ ኢትዮጵያዊያን የነገ ኢትዮጵያ ስለምታንሱ ለራሳችሁ ክብር ብላችሁ የኢትዮጵያን ክብር ለመጠበቅ ሁላችሁም መትጋት ይኖርባችኃል፡፡ ስድስተኛው ፅናት ነው በዚህ መከራ፣ በዚህ ችግር፣ በዚህ ክፉ ጊዜ ፅናት ያስፈልጋል፡፡ ምሩቃን ተማሪዎች እናንተ እድለኞች ናችሁ፡፡ ከብዙ ሚሊየን መመረቅ ችላችኃል ሳይመረቁ ሳይማሩ ያለፉ ብዙ አሉ ለኢትዮጵያ በፅናት መታገልና የነገን ኢትዮጵያ ብርሃን ለማምጣት መስዋዕት መሆንም ቢሆን ክብር መሆኑን አውቃችሁ በፅናት ለኢትዮጵያ ልማትና ለኢትዮጵያ ብልፅግና እንድትሰሩ በከፍተኛ ትህትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ሰባተኛው ህብር ነው፡፡ በዚህ ዩኒቨርሲቲ ዛሬ ሁለት ሺህ ሴተቶች ባይመረቁ፤ አካል ጉዳተኞች ባይመረቁ፤ ወንዶች እድሜአቸው ከ ሃያአምስት እስከ ሰላሣ ብቻ ቢሆን ምን ያክል ጉዶሎ እንደሚሆን አስቡት፡፡ የሴቶች አካል ጉዳተኞች የሰማንያውም ብሄር ብሄረሰቦች ተቀላቅሎ መመረቅ ከዚያም አልፎ ከጉረቤት አገራት አገራችንን እናንተን አምነውና ወደው ከናንተጋር ተምረው የተመረቁት ሰዎች መኖራቸውን ማየት እጅግ በጣም የሚያኮራና አስደሳች መሆኑን አውቃችሁ ለህብረትና ለመሰባሰብ ልባችሁን ክፍት አድርጉ፡፡ ዶ/ር ሐይሌ ፊዳ በፈረንሳይ በነበረው ቆይታ ከብረዘደንት አልፋ ኮንዴ

ጋር ክላስ ሜት ነበሩ። በጋራ ይማሩ ነበር። ፕሬዘደንት አልፋ ኮንዴ ኢትዮጵያ ሲመጣ የመጀመሪያ ጥያቄው ዶክተሩን እነ ንግስትንና የባሏን ቤተሰቦች የት እንዳሉና ማወቅና መጠየቅ እነዛን እንቁ ሰዎች አፍሪካ አጣች ብሎ ያስባል። ዛሬ ከእናንተ ጋር የተማሩ ነገ ቻይና አሜሪካ አውሮፓ ስትሄዱ የሚማሩ ሰዎች መድረሻቸው አይታወቅም። የእናንተም እንዲሁ። እናንተ ውስጥ ሳይንቲስቶች አሉ። ከእናንተ ውስጥ የሀገር መሪዎች አሉ። ከእናንተ ውስጥ ችግር የሚፈቱ ትላልቅ ጭንቅላቶች አሉ። ሌላውን ሰው ስታገኙት እናንተ ሳይንቲስት ከሆናችሁ እሱ ያገር መሪ መሆኑ አስባችሁ አክብራችሁ ተቀበሉት። የመጨረሻውና ስምንተኛው ትምህርት ለሂወት ነው። ትምህትር መነሻ እንጂ መድረሻ የለውም። ትምህርት አያበቃም ሁሌ ተማሪ መሆን ሁሌ ለመማር መዘጋጀት ከተፈጥሮ መማር እንዳለንብን ማሰብ ከሁላችን ይጠበቃል። ዛሬ ከየቤታችሁ ስትመጡ ያሽከረከራችሁበት መንገድ የሆነ አርሶ አደር መሬቱን ለቆ፣ የሆነ አክቴክት ዲዛይን አድርጉት፣ የሆነ ሲቪል ኢንጅነር አስፋልቱን ገንብቶት፣ የሆነ ኢኑቬተር መኪናውን ሰርቶ፣ መካኒካል አላልኩም ዲስ ቻርጅ እየሆነ ስለመጣ በብዙ ሰዎች መሰረትና ጥረት ላይ እየነዳችሁ እንደመጣችሁ አስባችሁ እናንተም ለትውልድ አዲስ መሠረት ለመጣል መነሳት፣ መዘጋጀት ይኖርባችኋል። ብቻውን ያለቀ ነግር የለም በአንደኛው መሰረትላይ ሌላ መሠረት እየጣልን ትውልድ በቅብብሎሽ የሚቀጥልበት ሀገር እንድትሆን አዲስ መሠረት፣ አዲስ ማንነት ለመገንባት ከልብ እንድትነሱ ያንን ማድረግ እንድትችሉ ምኞቴን ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ።

ውድ ተመራቂዎች በአንድ መርከብ የተሳፈሩ ሰዎች በተለያየ ክፍል ቢቀመጡም ያች መርከብ በአንድ አቅጣጫ መቅዘፏንና መጓዝዋን ማረጋገጥ አለባቸው ግማሹ ከላይ ግማሹ ከታች ግማሹ ከፊት ግማሹ ከኃላ ከተቀመጠ በተለያየ አቅጣጫ ቢቀዝፉ መርከቧ መድረስ ሚገባት ቦታ አትደርስም። እያንዳንዳችን የጋራ ታሪክ መፍጠር ካልቻልን ምሁራን በመካክራችሁ ተወያይታችሁ የማያስፈልገንን ትታችሁ የሚጠቅመንን የጋራ ታሪክ መፃፍ ትችላላችሁ። ምሁራን ተመካክራችሁ የሚጠቅመንን የጋራ ቪዥን ማስቀመጥ ትችላላችሁ። ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያ ደስትኔሽን ፕሮስፈሪቲ መሆኑን፤ ብልፅግና መሆኑን አምነን በአንድ አቅጣጫ መቅዘፍ ካልቻልን ያኮረፈ ሁሉ ወደ ቀበሌ ካለ ኢትዮጵያ ትንሽ ትሆናለች። ይህ እንዳይሆን መብራቱ ጨለማውን ገፎ መንገድ ማሳየት ሲገባው እራሱ ጨለማው ራሱ ብርሃኑ በጨለማ ተውጦ ብርሃን ማሳየት ከተሳነው ጉዞው ይደናቀፋል። የተማረው ያወቀው ለኢትዮጵያ መንገድ ማሳየት የሚገባው ተምሬአለሁ አውቄአለሁ ብሎ መንገድ የሚያጠፋና የሚያደናብር እንዳይሆን ማስተዋል፣ መመካከር፣ መወያየት፣ መደማመጥ እና ለሁሉ ህዝቦቻችን የሚበጀውን መንገድ መፍጠር ከእናንተ የሚጠበቅ ይሆናል።

በመጨረሻም የዛሬ ምሩቃን ውለታ አለባችሁ። የመጀመሪያው ውለታ ሳይማሩ፣ ጠግበው ሳይበሉ፣ መቀነታቸውን ፈተው ያስተማሩ ወላጅ ቤተሰቦች ናቸው። ወላጆቻችሁ ከእናንተ የሚፈልጉት የመጀመሪያው ነገር የእናንተን ስኬት ማየት ነው። ከስኬታችሁ በኃላ እንደ ኢትዮጵያ ባህል እነሱን መጦር፤ እንዳስተማሯችሁ የመጨረሻ ጊዜ አቸውን በደስታ እንዲያሳልፉ ማድረግ ከእናንተ ይጠበቃል። ወላጆቹን የዘነጋ አገሩን ማስታወስ አይችልም።

ሁለተኛው ውለታችሁ የመምህራኖቻችሁ ነው። መምህራኖቻችሁ በትውልድ ስፍራችሁ በኤልመንተሪ በሀይስኩል ያስተማሩዋቸው ሰዎች እናንተ ዛሬ ያላችሁን ወይም የምታገኙትን ድግሪ ከዛበላይ ያላገኙ ብዙ አሉ። እነሱ ቀልጠው እናንተን አሻግረዋችኋል። ዛሬ በዩኒቨርሲቲ የተማሩ ሰዎችም እናንተ ከምትደርሱበት ለመድረስ ብዙ ይቸገራሉ። የነሱ እያለቀ የእናንተ እየጀመረ ስለሆነ። ባለፋችሁበት መንገድ ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ረግጣችሁ ያለፋችሁበትን ድልድይ ማስታወስና ማመስገን ያስፈልጋል። ለምሳሌ ክረምት የገጠር ልጆች በእናንተ ትውልድ ስፍራ ያሉትን ኢልመንተሪ ስኩል ተማሪዎች አስተባብራችሁ ብታስተምሩ፣ ችግኝ ብትተክሉ፣ የጥገና ጉድለት ብትሳተፉ ለመምህራኖቻችሁ ውለታ እንደዋላችሁ ይቆጠራል።

ሶስተኛው የቀደምቶቻችሁ ውለታ ነው ቅድም እንዳነሳሁት የእኛ አንሲስተርስ መሠረት እየጣሉ ያቆዩትን ሀገር ማስቀጠልና ለትውልድ ማስረከብ ከእናንተ ይጠበቃል። በማንኛውም ጉዳይ ተከራከሩ፤ በማንኛውም ጉዳይ ተወያዩ፤ በማንኛውም ጉዳይ ተመካከሩ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን በሚመለከት ጉዳይ ላፍታም ቢሆን ለድርድር አታቅርቡ።

በመጨረሻም ያገር ውለታ አለባችሁ እናንተን ለማስተማር ቅድም ፕሮፌሰር እንዳለው ሳይሆን ኢትዮጵያ ካስቀመጠችው በጀት ትልቁን ያኖረችው ለትምህርት ነው። ይሄ ሁሉ ኃብት የምታፈሰው ተምረው ድህነትን፣ ችግርን፣ ርሃብን፣ እርዛትን አለመደማመጥን አለመሰልጠንን አስቀርተው ስልጡን ኢትዮጵያን ይፈጥሩልኛል የሚል እምነት ስላላት ስለሆነ እስካሁን ላስተማረች ኢንቨስት ላደረገች ሀገር በመስራት ብድራትዋን እንድትከፍሉ በዚሁ አጋጣሚ በትሕትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ ። አገር በፈተና ወቅት በመከራ ጊዜ በችግር ጊዜ ስቃይዋን የሚያበዛ ችግርዋን የሚያገዝፍ የማያውቁ ሰዎች ጩህት ሰዎች ሳይሆን የሚያውቁ ሰዎች ዝምታ ነው። የምናውቅ ሰዎች ዝም ካልን፣ የምናውቅ ሰዎች አይተን እንዳላየን ከሆን ዮፍታሔ ንጉሴ እንዳሉት; "አገሬ ተባብራ ካረገጠች እርካብ ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ የእንቧይ ካብ"።

አመሰግናለሁ